# ግጥምጥሞሽ

አብርሃም በየነ

የዚያች አገር ዜጋ ከንዋታ

ያለቅሳል አሉ መንታ መንታ

ግን በዕምባው ሾር ዳር አካልሎ

ይኮተኩታል ቂም አብቅሎ።

.......................................................

የአድዋው ፈላጭ ቆራጭ ከፍትህ የራቀ

የስልጣን ብልግናው መረን የለቀቀ

ጋምቤላን ጨፍጭፎ

አፋርን ሸራርፎ

ወሎን መሬት ዘርፎ

አምቦን ደም አጉርፎ

ጎንደርን አቅልጦ

ሸዋን በግፍ ድጦ

ጎጃም ብር ሸለቆ የበደል አዝመራ

ቂም ይሰበስባል በቀል እያፈራ።

..............................................

የፍትሁ መድሎ ጭቆና

ያወጣው ህግ ካቴና

ህዝብ ትንፍሽ እንዳይል በልጓሙ

አንደበቱ ታስሮ በዝሙ

ነገር ዓለሙ ይደንቃል

አፍ ታፍኖ ያለ ቃል

ጥርስ ከፍቶት ይስቃል።

............................................................

እንደ ዘመነኛው ቅጠል እንደ ጫቱ

ዘሮች ካፈር ወድቀው ቢሞቱ ቢሞቱ

ምነው አልሆን አሉ ፍሬአማ አዝእርቱ ?

...........................................................................

የሚለበልብ ሳማ

የሚዋጋ አቃቅማ

የሚኮሰኩስ አባ ጨጓሬ

የሚከነክን በርበሬ

አላበቅል ብሎ የመከነው መሬት

ህዝቡን አድርጎታል የማሌሊት ዝላይ

ማዘንበያ ማቶት።

.................................................................

በፀረ- ኢትዮጵያ ዘረኝነታቸው

መለስና ስዬን ምን አለያያቸው

ባንድ አልነበሩም ወይ አገር ያወቃቸው?

...........................................................................

ዶክተር ፕሮፌሰር ትልቅ የታፈረ

ፊደል የቆጠረ ምሁር የተማረ

ተድሜና ተቀለም ዕውቀት የገበየው

የክህደት ቁልቁለት ሲመራ እሚታየው

እርሱ ነው አድር ባይ ትልቅ ሰው ተብየው።

ዘወትር ጧት ማታ ላድማስ መጋረጃ

የምትዘርጊው ያ የወርቅ ግምጃ

ሰምዩና ምድሩ ያንቺው ግጥምጥሞሽ

ታይቶ እማይጠገብ ውብት አሽክሞሽ

ያይን ራብ አርጎሻል ሲነጋና ሲመሽ።

ጥቅምት 2005

........................//.................................